*በዶ/ር ኣበራ ሞላ*

# ኤድስ

ኤድስ ወይንም Acquired Immune Deficiency Syndrome (AIDS) በመባል የታወቀው በሽታ የሚመጣው ህዩመን ኢምዩኖደፊሸንሲ ቫይረስ Human Immunodeficiency Virus (HIV) በሚባል ጀርም ነው። በሽታው የሰውነትን የበሽታ መከላከያ በተለይ ነጭ ሴሎችን በማጥፋት ለቀላል በሽታዎች ለሕይወት ኣስጊ የመሆን ዕድል በመስጠት የሚገድል ነው። የሚተላለፈው ቫይረሱ ያለበት ሰው የተጠቀመበትን ያልፀዳ መርፌ በመጠቀም ወይንም ኣስፈላጊዎቹ ጥንቃቄዎች ሳይደረጉ በሚፈጸሙ የተለያዩ የግብረ ሥጋ ግንኙነቶች ነው። ኤድስን የሚያመጣው ሕይወት ያለው ጥገኛ ጠንቅ በኃይለኛ የማጉሊያ መሣሪያዎች ይታያል። ቫይረሱ ሰውነት ውስጥ እያለ እስከ ፳ ዓመታት የማይታመሙና በሽታውን የሚያስተላልፉ ጤነኛ ሰዎች ኣሉ።

የኤድስ በሽታ ሲጀምር ሰውነት ወይንም ኣካላችን በቀላሉ የሚከላከላቸው ጀርሞች እንደፈለጋቸው በመባዛት ለሕይወት ኣደገኛ ሆነው ይገኛሉ። ለምሳሌ ያህል ጤነኛ መድን በነበረን ጊዜ ከማይተናኮሉን ባክቴሪያዎች ኣንዱ ኒሞኒያ (Pneumonia) ያስከትላል። የቆዳ ካንሰር (Kaposi's Sarcoma) እና የኣንጎል በሽታም ሊኖሩ ይችላሉ። AIDS Related Conditions (ARC) ወይንም *ኣርክ* የሚባሉ ምልክቶችም ሊመጡ ይችላሉ። ከእነዚህም መካከል የንፍፊት ማበጥ፣ የማይለቁ ትኩሳቶች፣ ድካምና ተቅማጥ፣ ክብደት መቀነስ (ከ፲ በ፻ በላይ)፣ ደረቅ ሳልና ከባድ የእንቅልፍ ላብ ይገኙበታል። ትረሽ (Thrush) እና ሽንግልስ (Shingles) የሚባሉ በሽታዎችም ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል።

ኤድስ እንዳይዝ የምንከላከልበት የክትባት ዘዴ የለም። በሽታው ከያዘም በኋላ የሚፈውስ መድኃኒት የለም። በኣሁኑ ጊዜ ያለን መከላከያ በበሽታው እንዳንያዝ ኣስፈላጊዎቹን ጥንቃቄዎች ማድረግ ብቻ ነው። በሽታው እንዴት እንደሚተላለፍ በምርምር የተደገፉ መረጃዎችን በመከታተል ተረድቶ ቫይረሶቹ እንዳይሰራጩ ትክክለኛዎቹን ጥንቃቄዎች መከተልና ለሌሎችም ማስተማር የእያንዳችን ኃላፊነት መሆን ይገባል። ኤድስ ኣሰቃቂና ኣደገኛ በሽታ ቢሆንም እንደጉንፋን በቀላሉ የሚተላለፍ ስላልሆነ ልንከላከለው የምንችለው በሽታ ነው። ስለ በሽታው በሰፊው ማወቅ ባንፈልግ እንኳን በበሽታው እንዳንያዝ እንዴት እንደምንከላከል መረዳትና ወደ ሌሎች እንዳይተላለፍ እንዴት እንደምንጠነቀቅ ማወቅ እንደሚጠቅሙ ተረጋግጧል።

ኤድስ ቀስ በቀስ እየተስፋፋ የመጣው ከ1978 (፲፱፻፸ ዓ.ም.) ወዲህ ሲሆን እስከ 1985 ድረስ የተበከለ ደም በመወጋትና በመሳሰሉት ብዙ ሰዎች ያለቅብጠታቸውም በበሽታው ተይዘዋል። ከ1988 ወዲህ ግን ኤድስ ሲይዝ ነጭ ሴል የሚሠራውን ኣንቲቦዲ (Antibody) በመመርመር የኤድስ ቫይረስ እንዳጋጠመን የሚጣራበት ፈጣን የምርመራ ዘዴ ስለተሠራ በተለይ የደም ማነስን ለመከላከል ሆስፒታል ከሚሰጠን ደም በመተላለፍ ሊይዝ የሚችለው ኤድስ ወደ መጥፋቱ ደርሷል።

ኤድስ በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊተላለፍ ይችላል።

- ቫይረሱ ያለበት ሰው የተጠቀመበትን የድረግ (Drugs) መርፌ ሌላ ሰው ቢጠቀምበት (Intravenous) በቫይረሱ መተላለፍ የተነሳ በበሽታው መያዝ ይቻል ይሆናል።

- በበሽታው ከተያዘ ወይንም ቫይረሱ ካለበት ማንኛውም ሰው (ወንድ ወይም ሴት) ጋር የግብረ ሰዶም ግንኙነት (Homosexual, Bisexual intercourse) በማድረግ በሽታው ሊይዝ ይችላል።

- ኤድስ ቫይረሱ ወይም በሽታው ካለበት ሰው ጋር በሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት (Heterosexual intercourse) የሚይዝ የኣባለ ዘር በሽታ ሆኗል።

- ቫይረሱ ያለባት እናት በሽታውን (ማህፀን ውስጥና በምትወልድበት ጊዜም) ለሕፃንዋ ማስተላለፍ (Intrauterine, Perinatal) ትችላለች።

- በበሽታው የተያዘች እመጫትን የጡት ወተት በመጥባት (በመጠጣት) (Oral) ሕፃናትን በሽታው ሊይዛቸው ይችላል።

ከኤድስ በሽታ ለመከላከል የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ይጠቅማል።

- ከማንኛውም ዓይነት የግብረ ሥጋ ግንኙነት (ከተቻለ) መቆጠብ፣ ወይንም ቫይረሱ ካሌለበት አንድ ታማኝ የፍቅር ጓደኛ ሌላ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ኣለማድረግ።

- ለረዥም ጊዜ ተማምነው ኣብረው የቆዩ ባልና መስጋትና ለኤድስ ሲባል በኮንዶም (Condom) መጠቀም የለባቸውም። ታማኝነት ከመቼውም ጊዜ ኣሁን ኣስፈላጊ ነው ።

- የሚወጉ ድራጎች (እየተደበቁ ተሰባስበው ባልፀዱ መሣሪያዎች ከሚወስዱ ጋር) አለመውሰድ። በሽታው ከያዘው ሰው ጋር መርፌና ሲሪንጋ ኣለመጋራት።

- ከማያውቁት ሰው ወይንም ከብዙ ሰዎች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት በማድረግ ከቆዩ (ኣመንዝራ) ጋር ማንኛውንም ዓይነት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ኣለማድረግ።

ቫይረሱ እንዳሌለበት ከማያውቁት (ወይንም በሽታው ከያዘው) ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ ካስፈለገ የሚከተሉትን ፬ ጥንቃቄዎች ማድረግ ያስፈልጋል።

- የኤድስ ቫይረስ ያለባቸው የተለያዩ የኣባለ ዘር ፍሳሾች (Semen, Vaginal secretions) ወደ ሌላ ሰው (ብልት፣ ኣፍ፣ ፊንጢጣ ወዘተ...) እንዳይገቡ መጠንቀቅ።

- የኤድስ መኖር ካጠራጠረ የግብረ ሥጋው ግንኙነት ከመጀመሩ በፊት ወንድየው የላቴክስ (Latex) ላስቲክ ኮንዶም ብልቱ ላይ ማድረግ ኣለበት። ከቆዳ (Skin) የሚሠራው ዓይነት ኮንደም ለኤድስ መከላከያ ኣይሠራም።

- ለተጨማሪ ጥንቃቄ እስፐርሚሳይድስ (Spermicides) ቫይረሶቹንም የመግደል ጥቅም ስላላቸው የኮንዶሙን ውጭና ጫፍ ማነካካት ሳይጠቅም ኣይቀርም።

- ከደረቁ ይልቅ ቅባት (Lubricant) ያለው የላቴክስ ኮንዶም እንዳይቀደድም ይመረጣል ። በውሃ (Water-base) በተበጠበጡ እንጂ እንደ ቫስሊን የአሉ በነዳጅ ዘይት የሚበጠበጡ (Oil-based) ቅባቶች ኮንዶሙን ስለሚበሳሱት አለመጠቀም ጥሩ ነው። ፓኬቱ ላይ የተጻፈውን ማንበብ ያስፈልጋል። ከፈቃደ ሥጋው ግንኙነት በኋላ ላቴክሱን በጥንቃቄ ማውጣት መረሳት የለበትም።

በተጨማሪም የሚከተሉት ታውቀዋል ።

- የአንድ ሰው ደም ወደ ሌላው (በብዛት) ሊተላለፍባቸው የሚችልባቸውን ቁሳቁስ ለሌላ ከማዋስ መቆጠብ። ለምሳሌ ያህል የጺም መላጫ፣ ጥርስ ብሩሽና መፋቂያ የመሳሰሉትን አለመዋዋስ። (ደም መበካከልን ሊያስከትሉ የሚችሉ ባህሎች ከአሉ ማረም ወይንም እንዲጠፉ ማበረታታት።)
- የኤድስ ቫይረስ ሊኖርባቸው የሚችሉ ደምና የመሳሰሉትን ጓንት (እና እንዳስፈላጊነቱም ማስክ) ሳያደርጉ አለመነካካት።
- ስለበሽታው ለማያውቁት ማስማትና ልጆች ማስተማር (Education) እንዲሁም ኤድስ ያለባቸውን በሚቻለን ሁሉ የመርዳት ኃላፊነትና በየጊዜው የሚገኙትን የምርምር ውጤቶች ለማወቅ መሞከርና ይሀንኑ ዕውቀት ማሰራጨት አለብን።
- የኤድስ ቫይረስ ደካማ በመሆኑ ከአካል ውጭ ለረዥም ጊዜ አይኖርም። (እንደ ዕቃው ዓይነት የተነካኩትን ለዓሥር ደቂቃዎች ማፍላት ወይንም አንድ በመቶ ብሊች ባለው ውሃ መዘፍዘፍ ቫይረሶቹን ሊገድል ይችል ይሆናል።)
- አንድን ሰው የበሽታው ቫይረስ እንዳላጋጠመው በተለያዩ (ተደጋጋሚ) የደም ምርመራዎች ማጣራት ይቻላል። (አስቀድሞም የአካባቢውን የኤድስ ሕግ ማወቅ ጠቃሚ ነው።)
- ኤድስ በመጨባበጥና በመሳሳም እንዲሁም በሽንትና በሰገራ፣ በወባ ትንኝና ቁንጫን በመሳሰሉ ደም መጣጮች አይተላለፍም ተብሏል።
- የኤድስ ቫይረስ (እራሱን ስለሚቀያይር ጥሩ ዓይነት) የመከላከያ ክትባት በቅርቡ ላይሠራ እንደሚችል ተተምኗል። የቫይረስ በሽታዎችንም ማዳን በጣም ከባድ ስለሆነ (የኤድስም ቫይረስ ከሰው ጂን ጋር ስለሚካለስ) ፈዋሽ መድኃኒት በቅርቡ መገኘቱ ያጠራጥራል ይባላል። እስከዚያው ድረስ ግን በሽታው በየአገሩ (ኢትዮጵያ ጭምር) መስፋፋቱን ስለቀጠለ ለሞት ከመማቀቅ አስቀድሞ ማወቅ የሚሻል ይመስለኛል። ቫይረሱ (ለረዥም ጊዜ) ከነበረባቸው መካከል ፺፱ በ፻ በበሽታው ተይዘዋል።
- AZT (ኤዚቲ) እና የመሳሰሉት መድኃኒቶች ቫይረሱ እንዳይባዛ በመከላከል በሽታው እንዳይገድል ጊዜ ለመግዛት ይጠቅማሉ ይባላል።
- የኤድስ መኖር ካጠራጠረ በጥሩ ጤንነት ለመኖር መሞከርና መድንን ከሚያዳክሙ መቆጠብ እንደሚራዱ ተገምቷል።

በሽታው በመካከላችን ስላለ ባለማወቅና በጥንቃቄ ጉድለት በኤድስ ብንያዝ ጥፋቱና ፀፀቱ የራሳችን ይመስለኛል። እስካሁን (1991) በዩናይትድ እስቴትስ ውስጥ የኤድስ ቫይረስ ከተገኘባቸው ፪፻፸ ሺህ ሰዎች መካከል ፩፻ ሺህ (፩፬፬,፬፬፬) በበሽታው ሞተዋል። በዓለም ላይም (፩፷፬) ኣገርች ፩ ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች በኤድስ በሽታ ተይዘዋል። (ሕዝቡም መጠንቀቅ ካልጀመረ በቫይረሱ የሚበከለው ሰው ቁጥር በየዓመቱ እጥፍ እየሆነ ሊቀጥል እንደሚችልና ለማስታመምም ብዙ ቢሊዮን ዶላርስ እንደሚያስፈልግ ተገምቷል።) ግብረ ሰዶም የሚያዘወትሩና ድረግ የሚወጉ ሰዎች በሽታ ነው እየተባለ ቸል ሲባል ቆይቶ ኣሁን የሁላችንም ጠር መሆኑ ስለተደረሰበት የሚፈለግብንን ብናከናውንና (ከመንግሥታት ጋርም) ብንተባበር በሽታውን መቆጣጠር (Control) ይቻል ይሆናል። የፈንጣጣን በሽታ ከዓለም ለማጥፋት (Eradication) ከጠቀሙን መካከል ክትባትና የሕዝቡ ትብብር ዋናዎቹ ናቸው።) ስለ ግብረ ሥጋ (Sexual) ግንኙነት ማውራት ለማንኛውም ሕብረተ ሰብ ኣሳፋሪ ቢሆንም ኤድስ ያመጣብን ዱብ-ዕዳ የሕይወት ጉዳይ ስለሆነ መወያየት መጀመር ኣለብን።

ይህ ጽሑፍ የተጻፈው የሕክምና ዕርዳታ ለመስጠት ኣይደለም። በበለጠ ለመረዳት ሐኪሞቻችሁን ኣማክሩ። በ1988 ለእያንዳንዱ የዩናትይትድ እስቴትስ ቤት ሰብ *Understanding AIDS* የተባለ ፰ ገጽ ጽሑፍ ከU.S. Department of Health ሲላክ ለእኔም እንደደረሰኝ ወደ ዓማርኛ ተርጉሜ ለሚፈልጉት መላክ እንዲቻል ጠይቄ በጀት ስላልተመደበለት ያቀድኩት ኣልተሳካልኝም ነበር። የእዚህ ጽሑፍ መነሻ ይህው የHSS Publication No. (CDC) HHH 88-8404 ነው። ይኸንን የዓማርኛ ጽሑፍ ማንም እንደፈለገው አባዝቶ ማሰራጨት ይችላል።

---

ዶክ | ኤችቲኤምኤል | ፒዲኤፍ

**AIDS CLOCK**